# ዛሬም ጀግኖች ያስፈልጉናል

(በአዲሱ አረጋ ቂጤሳ) email - doranielemo1974@gmail.com

**መግቢያ**

የጀግንነት ፍቺ ብዙ አሻሚ አይመስለኝም፡፡ ጀግና ማለት በሃገር ፍቅር ለአላማ የቆመ፣ የቆመለትን አላማ ለማሳካት ሌት ተቀን የሚተጋ፣ ለአላማዉም ዉድ ህይወቱን ሳይሰስት ለመሰዋት የወሰነ፣ ያመነበትን አላማ ከግብ ለማድረስ በሚያደርገዉ ትግል እና መስዋዕትነትን ለመክፈል ባለዉ ጽናት ለሌሎች አርአያ መሆን የቻለ ማለት ነዉ፡፡ ጀግንነት በሃገር ፍቅር ስሜትና በራስ ፍላጎት ጠላትን በመጋፈጥ ራስን ለመስዋዕትነት የማቅረብ ቁርጠኝነት ነዉ፡፡ ጀግንነት የሚገለጹባቸዉ መንገዶች የተወሰኑ አይደሉም፡፡ በማህበራዊ፣በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣በንግድ፣ በፖለቲካ፣ በሰላም ወዘተ እንቅስቃሴ ሁሉ ሃገራዊ ፍቅርን መግለጽና የሃገር ክብርን መጠበቅ ይቻላል፡፡ በሀገራችን በጦርነትም ሆነ በሰላም ጊዜ በሃገር ፍቅር ስሜት የነደዱ፣ ሀገራቸዉን ከተጋረጠባት ችግር ለማላቀቅ ለብሄራዊ ክብራችን ሲሉ በየትግል መድረኩ በመስዋዕትነት የተወለዱ በዛሬዉ ህይወታችን ዉስጥ እጅግ የምናከብራቸዉና አርአያነታቸዉ የጎላ የተዘመረላቸዉመም ያልተዘመረላቸዉም ብዙ ጀግኖች አሉን፡፡ የዚህ አጭር ጽሁፍ አላማ የጀግንነት ፍቺ እና ንድፈ ሃሳብ መተንተን አይደለም፡፡ እንደሀገር ዛሬም ትልቅ ጠላት ከፊታችን ስላለ የትዉልዱ ጀግኖች እንደሚያስፈልጉን ለማቅረብ ነዉ፡፡

**ጀግንነት በኢትዮጵያ -ትናንት**

የሃገራችን ታሪክ ባብዛኛዉ የጦርነት ታሪክ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዉጭ የጠላት ወራሪዎች ሃይሎች ጋርም ሆነ እርስ በርስ ብዙ ተዋግተናል፡፡ (የእርስ በርስ ጦርነታችንን በተመለከተ ሌላ ግዜ በሌላ ርዕስ እንመለስበታለን) ከወራሪ ሃይሎች ጋር በርካታ ጦርነቶችን አድርገናል፡፡ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን ከእንግሊዞች ጋር ተዋግተናል፡፡ አጼ ቴዎድሮስን፣ ገብርዬንና ሌሎች በርካታ የጦር ሜዳ ጀግኖችን በልባችን ከትበናል፡፡ በአጼ ዮሐንስ ዘመን ከደርቡሾች ጋር ተዋግተናል፡፡ የአጼ ዮሐንስ፣ የራስ አሉላን፣ የባሻ አዉአሎምን አርአያነት እና መስዋዕትነት በልባችን አስቀምጠናል፡፡ በአድዋ ጦርነት ወራሪዉን ሀይል ድል በመንሳት በኢትዮጲዊ አንድነትና አልደፈር ባይነት ገድላችን ለጥቁር ህዝቦች የነጻነት ምሳሌ ሆነን ጀግንነታችንን አረጋግጠናል፡፡ በዳግም በኢጣሊያ ወረራ ወቅት በነአብዲሳ አጋ፣ በባልቻ ሰፎ፣ በዘርዓይ ደረስ፣በአቡነ ጴጥሮስ፣ በበላይ ዘለቀ፣ በበቀለ ወያ፣ በአበበ አረጋይ፣ በገለታ ቆርቾ፣ በገረሱ ዱኪ፣በሃይለማርያም ማሞ፣ በዑመር ሰመተር፣ በጀገማ ኬሎ፣ በከበደ ብዙነሽ፣ ሸዋረገድ ገድሌ እና

በበርካታ ስማቸዉን ባልጠቀስኳቸዉ ጀግኖች አርበኞች ልባችን ኮርቷል፡፡ በሶማሊያ እና በኤርትራ ወረራ ወቅቶችም ጀርባቸዉን ሳይሆን ግንባራቸዉን ለጥይት ሰጥተዉ የተሰዉ ፣ ለአላማቸዉ ሞተዉ የሃገርን ልዑዋላዊነት ያረጋገጡ የኢትዮጲያ የጦር ሜዳ ጀግኖች ተቆጥረዉ አያልቁም፡፡

በሃገራችን የስርአት ለዉጥ እንዲመጣ፤ ጭቆናና አድሎ ተወግዶ በምትኩ ሰላም፣ ዴሞክራሲና እኩልነት እንዲሰፍን ተራራን ከሚያክል ሥርዓት ጋር የተፋለሙና የተሰዉ እነ ጥላሁን ግዛዉ፣ እነማርታ፣ እነዋለልኝ፣ እነ ሙሴ፣ እነአገሪ ቱሉ፣ እነ ኮበል፣ እነ አሞራዉ… ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከጦር ሜዳዎች ዉጭም የሀገራችን ጀግኖች ብዙ ናቸዉ፡፡ አበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ፣ ዋሚ ቢራቱ፣ ምሩጽ ይፍጠር፣ ፋጡማ ሮባ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ሃይሌ ገብረስላሴንና ሌሎችን በስፖርት ዘርፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ አቤ ጉበኛ፣ በዓሉ ግርማ፣ ከበደ ሚካኤል፣ ዮሀንስ አድማሱ፣ኦነስሞስ ነሲብ፣ ጸጋዬ ገብረመድህንና ሌሎችን በስነጽሁፉ ዘርፍ መዘርዘር ይቻላል፡፡ በሙዚቃ፣ በስዕል፣ በትወና፣ በጋዜጠኝነት፣ በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ እና በሌሎች የሙያ መስኮችም በዚህች አጭር ጽሁፍ ተዘርዝረዉ የማያልቁ በርካታ ጀግኖች ተወልደዉ ለዓላማቸዉ በጽናት ታግለዉ፣ የሃገራቸዉንና የህዝባቸዉን ጠላቶች ፊት ለፊት ተጋፍጠዉ አስፈላጊዉን መስዋዕትነት በመክፈል በትዉልድ ልብ ዉስጥ የዘለአለማዊነትን ሀዉልት ተክለዉ አልፈዋል፡፡

## ኢትዮጵያ ዛሬም ጀግኖች ያስፈልጓታል

የትናንት የኢትዮጲያና የህዝቦቿ ጠላቶች የዉጭ ወራሪ ሃይሎች እና ጨቋኝ ገዢዎች እንደነበሩ አይተናል፡፡ እነዚህን ጠላቶች ለማስወገድም በርካታ የጦር ሜዳ እና የፖለቲካ ጀግኖች ተፋጥረዉ አላማቸዉን አሳክተዉ ለዛሬ አብቅተዉናል፡፡ በትናንት ጀግኖች ክቡር መስዋዕትነትም ዛሬ ቀና ብለን መሄድ ችለናል፡፡ በትከሻቸዉ ላይ ቆመን ዘለግ ብለን ታይተናል፡፡ ሰላም እና ነጻነትን አግኝተናል፡፡ ዛሬስ? ዛሬ በርግጥ የሚያሰጋን የዉጭ ወራሪ ወይም ጨቋኝ የሆነ ስርዐት የለም፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ሲያቸግሩን ከነበሩት ጠላቶች ባልተናነሰ ሁኔታ የሚያሸማቅቀን፣ በአለም አደባባይ አንገት የሚያስደፋን፣ አንድነታችንንና ሰላማችንን ሊፈታተን የሚችል ትልቅ ጠላት በኢትዮጲያና በህዝቦቿ ፊት ተደቅኗል፡፡ ድህነት!! ዛሬ ሃገራችን ዋነኛ ጠላቷ የሆነዉ ድህነትን በጽናት የሚፋለምላትና ድል የሚጎናጽፉት ጀግና ትፈልጋለች፡፡ ድህነትን ለማሸነፍ ኢትዮጲያ ክተት ካወጀች ሰነባብታለች፡፡የትዉልዱ የሰላም ሜዳ ጀግኖችም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ በርግጥ የጸረ ድህነት ፍልሚያዉ እንደ ጸረ ጭቆናዉና ጸረ ወረራዉ ፍልሚያ የደም እና የህይወት

መስዋዕትነትን አይጠይቅም፡፡ እሱ በትናንት ጀግኖች ተከፍሏልና፡፡ ዛሬ የሰላም ሜዳ ጀግኖች ያስፈልጉናል፡፡ የደምና የአጥንት ሳይሆን የላብ እና የእዉቀት መስዋዕትነት ከፍለዉ ከድህነት የጭቆና መንጋጋ አርነት የሚያወጡን የሰላም ሜዳ ጀግኖች፡፡

ዛሬ የሚያስፈልገን ጀግና ገበሬ ነዉ፡፡በበአላት አሳብቦ ሙሉ ግዜዉን እርሻዉ ላይ የማያሳልፍ፣ በየጠላ ቤቱ ሲዞር እርሻዉን በአረም እና በተባይ አስበልቶ ለእርዳታ እጁን የሚዘረጋ፣ ድህነት ጋር የተላመደና ከድህነት ጋር ታርቆ መኖር የሚፈልግ ገበሬ ሳይሆን፣ በድህት ላይ ያመጸ ‹‹ዘራፍ ለሃገሬ!›› ብሎ የተነሳ ፣ በማሳዉ ላይ ሌት ተቀን የሚተጋ፣ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነቱን የሚያሳደግ፣ ባመረተዉ ምርት ልጆቹን እና ሸማቹን የሚያጠግብ፣ ልጆቹን ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት የሚልክ፣ ምርቱን ሽጦ በሚያገኘዉ ገቢ ቆጥቦ ሕይወቱን ለማሻሻል ሌት ተቀን የሚተጋ ጀግና ገበሬ ያስፈልገናል ፡፡ ሀገራችን በረሃብና በቸነፈር ሳይሆን የዳቦ ቅርጫት ሆና በአለም አደባባይ ቀና እንድንል የሚያደርገን ይህ ነዉና!! ኢትዮጲያ ዛሬ ሚሊዮን ጀግና ገበሬዎችን ትፈልጋለች፡፡

ዛሬ ኢትዮጲያ ጀግና ምሁራን ያስፈልጓታል፡፡ በርበሬ እና ሽሮ ተወደደብኝ ብሎ የሚያማርር ምሁር ሳይሆን፣ ከ‹‹ተራዉ›› የህብረተሰብ ክፍል በአስተሳሰብ ደረጃዉ ምንም የማይለይ ቀለማዊ ምሁር ሳይሆን፣ በ1960ቹ የጽንፍ ፖለቲካ የታወረና ‹‹ሃሳቤን ያልተቀበለ ሁሉ ጠላቴ ነዉ ብሎ›› የሚያምን ምሁር ሳይሆን፣ በጭፍን ድጋፍ እና በጭፍን ተቃዉሞ የታጠረ አድሃሪ ምሁር ሳይሆን ፣ ችግሮችንና ድክመቶችን ብቻ እየተከታተለ በመዘርዘር የሚያማርር ጨለምተኛ ምሁር ሳይሆን ሀገሪቷን ከተጋረጠባት የዘመኑ ጠላት ድህነትን የሚጋፈጥ፣ የጸረ ድህነት ትግሉን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሃሳቦችን የሚያመነጭ፣ የተጀመረዉን የጸረ ድህነት ትግል በጥናትና ምርምር የሚደግፍ፣ መላ ህብረተሰቡን በምሁራዊ እዉቀቱ አሳምኖ አነቃንቆ ድህነት ላይ የሚያዘምት ጀግና ምሁር ያስፈልገናል፡፡ በድህነት ላይ ‹‹ዘራፍ ለህዝቤ!›› ብለዉ የተነሱ ምሁራን በመቶ ሺህዎችና በሚሊዮኖች ያስፈልጉናል፡፡ የኛ ምሁራን ከጀገኑልን ኋላቀነትና ድህነት በቶሎ ተሸንፎ ስልጡንና ጠንካራ ህዝብ መሆናችን አይቀሬ ይሆናልና!

ዛሬ ጀግና ፖለቲከኞች ያስፈልጉናል፡፡ ‹‹ወይ ሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ›› የሚል አስተሳሰብ ያለዉ ጽንፈኛ የዜሮ ድምር ፖለቲከኛ ሳይሆን፣ ከህዝብ ጥቅም ይልቅ የራሱን ጥቅም የሚያስቀድም ሌባ ፖለቲከኛ ሳይሆን፣ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነዉ በሚል አባዜ በሃገር ጥቅም በተጻራሪ የሚቆም ፖለቲከኛ ሳይሆን፣ የህዳሴዉ ግድብ፣ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አይሳካም ብሎ የሚያሟርት ስልብ የመንደር ፖለቲከኛ ሳይሆን፣ የሃሳብ ልዩነቱን በሃሳብ ማስታረቅ አቅቶት በቦክስ የሚቃመስ ፖለቲከኛ ሳይሆን፣ የሰከነ ዴሞክራሲያዊ አሰተሳሳብ ያላዉ፣ ስልጡንና ልዩነቱን በሰላማዊ የሃሳብ ትግል የሚያራምድ፣ ሀገርን የሚጠቅም አማራጭ

ሃሳብ ማመንጨት የሚችል፣ የሀገርን ብሄራዊ ጥቅም ከፓርቲ ጥቅም ለይቶ የሚያዉቅና በብሄራዊ ጥቅም የማይደራደር፣

ሕገመንግስቱን የሚያከብርና የሚያስከብር፤ ጀግና ፖለቲከኛ ያስፈልገናል፡፡ እንደዚህ አይነት ጀግና ፖለቲከኞች በመቶ ሺህዎች ያስፈልጉናል፡፡ ፖለቲከኞቻችን ከጀገኑልን በድህነት እና በኋላ ቀርነት ሳይሆን በዳበረ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህል በዓለም ዘንድ መታወቃችን አይደል!?

ዛሬ ጀግና የጥበብ ባለሙያዎች ያስፈልጉናል፡፡ በስጽሁፋቸዉ፣ በድርሰታቸዉ፤ በዘፈናቸዉ በአጠቃላይ በጥበብ ስራቸዉ ስለጾታዊ ፍቅር ብቻ የሚሰብኩ፣ የፈረንጆችን የጥበብ ስራዎች ቀድተዉ የራሳቸዉ አስመስለዉ የሚያቀርቡ ሳይሆን በጥበብ ሙያቸዉ የህብረተሰባችንን ንቃተ ህሊና ለማሳደግ የሚተጉ፤ በማንነታቸዉና በባህላቸዉ የሚኮሩ፤ በጥበብ ሙያቸዉ ታታሪ ህዝብ እንዲፈጠር ትዉልድን ለመቅረጽ የሚተጉ አርአያነት ያላቸዉ በርካታ የጥበብ ባለሙያዎች ያስፈልጉናል፡፡ትናንተ በጥበብ በቀረርቶ እና በሽለላ ተነሳስተን ወራሪዎችን ድባቅ እንዳደረግን ሁሉ በጥበብ ሥራዎቻቸዉ ደህነት ላይ የሚያነሳሱን፤ለሃገር ልማትና ገጽታ ግንባታ የሚተጉ ጀግና የጥበብ ባለሙያዎች ያስፈልጉናል፡፡ በድህነት የተበላሸዉ ገጽታችን የሚገነባዉ በጥበብ ስራዎች ነዉና!

ዛሬ ጀግና ወጣት ያስፈልገናል፡፡ ሳይሰራ የሚበላ ‹‹ወጣት ጡረተኛ›› ሳይሆን፤ በጫት ፣በመጠጥና በአደንዛዥ ዕጾች ሱስ የናወዘ፣ ማንነቱን የረሳ፣ ከድህነት ተላምዶ በቢዮንሴና እና በኢንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ፋንታሲ ዉስጥ የሚኖር ወጣት ሳይሆን፣ከድህነቱ ይልቅ የቢዮንሴ ክብደት መጨመር እና የአርሴናል መሸነፍ የሚያንገበግበዉ ወጣት ሳይሆን ፤ የምግብ ሜኑ እንጂ መጽሃፍት ማንበብ የማይወድ ወጣት ሳይሆን፤ በየዩኒቨርሲቲዉ ‹‹የብሄሬ/የሃይማኖቴ ተከታይ ተሰደበ›› ብሎ በቡድን በድንጋይ የሚደባደብና ከመንጋ አስተሳሰብ ያልተላቀቀ ወጣት ሳይሆን፣ የፈረንጅ ወጣቶችን ጥበብ እና ክህሎት ትቶ አለባበሳቸዉንና የጸጉር እስታየላቸዉን ብቻ የሚኮርጅ ቂል ወጣት ሳይሆን፣ አክሱም ሀዉልት፣የጎንደር ግንቦች፣ ላሊበላ ዉቅር አቢያተ ክርስቲያናት፣ ድሬ ሼክ ሁሴን፣ የአባጅፋር ቤተ መንግስት፣ የጢያ ትክል ድንጋዮችንና የትናንት ጀግኖች የእጅ ስራ ዉጤቶችንና ሌሎች ታሪካዊ ቅርሶችን ለፎቶግራፍ ማዳመቂያ ብቻ የሚያዉል ነገር ግን ‹‹እኔስ ለሃገሬ ምን ሰራሁ?›› ብሎ ራሱን የማይወቅስ ወጣት ሳይሆን፤ ጥራዝ ነጠቅ ኢንግሊዘኛ ስለቻለ ራሱን ጀግናና ሊቅ አድርጎ የሚቆጥር ቦቅቧቃና ደንቆሮ ዌስተርናይዝድ ወጣት ሳይሆን፤ ፌስ ቡክ ላይ ተጥዶ የሚዉል የሙሉ ግዜ አሽሟጣጭና ተቺ ስራፈት ወጣት ሳይሆን፣ በራሱ የሚተማመንና የሚኮራ፣ በሰለጠነ የአስተሳሰብ ትግል የሚያምን፣ ስራን የማይንቅ፣ ራሱን በዕዉቀት ለማነጽ የሚተጋ ፣ድህነትን አምርሮ የሚጠላና ከድህነት ራሱንና

ሀገሩን ነጻ ለማዉጣት በቁጭት የተነሳ ባለሻካራ መዳፍ ጀግና ወጣት ያስፈልገናል፡፡ ጊዜዉን ባግባቡ የሚጠቀም፣ በምክኒያት የሚደግፍ እና በምክኒያት የሚቃወም፣ ለትናንትናዎቹ ጀግኖች ሰማዕታት ድህነትን በማሸነፍ ህያዉነታቸዉን ለማረጋገጥ ‹‹ዘራፍ ጀግና የጀግና ልጅ!›› ብሎ ቆርጦ የተነሳ ወጣት ያስፈልገናል፡፡ ድህነትን ለማሸነፍ በጀግንነት የተነሱ ሚሊዮን ጀግና ወጣቶች ያስፈልጉናል፡፡

## ማጠቃለያ

እያንዳንዱ ትዉልድ የራሱ የጀግንነት ገድል አለዉ፡፡ በታሪክ አጋጣሚ የጦር ሜዳ ጀግንነት የህይወት ጥሪያቸዉ የነበረዉ የትናንት ጀግኖች ከወራሪዎችና ከጨቋኞች ጋር በመፋለም የጀግንነት ገድላቸዉን በደማቸዉ ጽፈዋል፡፡ የዛሬ ትዉልድም በሰላማዊዉ ሜዳ ጀግንነትን የሚጠይቅ ታሪካዊ ፍልሚያ ከፊቱ ይጠብቀዋል፡፡ ሀገራችንን የሚያዋርድ ክፉ ጠላት ድህነት ከፊታችን ቆሟል፡፡ የዛሬዉ ትዉልድ እንደትናንትናዎቹ ጀግኖች በሃገር ፍቅር ወኔ በጀግንነት ከተነሳን፣ በተሰማራንበት የስራ መስክ በቁርጠኝነት በመነሳት የሚጠበቅብንን ከተወጣን፣ ድህነትን አሸንፈን ገድላችንን በላባችን እንጽፋለን፡፡ የትናንት ጀግኖቻችንን ህያዉነት እናረጋግጣለን፡፡ እኛም በነገዉ ትዉልድ እንዘከራለን፡፡